# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

የአሥራ ሁለተኛ ሰንበት (እሑድ) ሥርዓተ አምልኮ

ከሰኔ ፲፯ እስከ ፳፭ «አስተምህሮ» ይባላል።
ሰኔ ፳ ቀን ሐነጽዋ ይባላል።

## የዕለቱ ምስባክ

አንተሰ እግዚኦ መሐሪ ወመስተሳህል
ርሁቀ መአት ወብዙኃ ምህረት ወጻድቅ
ነጽር ላእሌየ ወተሣሃለኒ

አቤቱ አንተ ግን መሐሪና ርህሩህ አምላክ ነህ
መአትህ የራቀ ምሕረትህም እውነትህም የበዛ
ወደኔ ተመልከት አድነኝም

መዝ ፹፭፥፲፭

ወንጌል፡ ማቴ ፳፪፥፩-፳፩
ቅዳሴ፡ የጌታችን ቅዳሴ

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ናክብር ሰንበቶ
ሰንበትን እናክብር

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ሮሜ ፭፥፲፪-ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ዮሐ ፬፥፩-ፍጻሜ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፲፮፥፩-፱ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ትምህርት

### የንጉሡ ሠርግ

ማቴ ፳፪፥፩-፲፬ ያንብቡ ምሳሌውም በማቴዎስ ፳፩ ላይ አይሁድ ካህናት ፈሪሳውያን በክርስቶስ ላይ ያደረሱትን ተቃውሞ የሚያመለክት ነው። ልክ ማቴዎስ ፳፩፣ ፴፫-፵፬ እንደተገለጸው ምሳሌ ማለት ነው። መድኃኒታችን የወንጌልን ነገር፣ በወንጌል፣ በክርስቶስና በክርስቲያኖች መካከል ያለውን ሕብረት ለመግለጥ የአይሁድንም አለማመንና ጥፋት በሚከተለው ምሳሌ ገለጠው።

ምሳሌውም አንድ ንጉሥ ለልጁ ሠርግ አደረገና ለሠርጉ የታደሙትን (በንጉሡ ልብ የታወቁትን) ወደ ሠርጉ እንዲጠሩ አሽከሮችን ላከ፤ ሁሉም አመካኙ፤ አንዱ በመሬቱ ሌላው በንግዱ፣ ሌላውም በሚስቱ፣ ሌላውም በመሰለው እያመካኙ አንመጣም አሉ (ሉቃ ፲፬፥፲፮-፳፬ ። ማቴ ፳፪፥፫)፤ ሁለተኛም ባሮቹን ልኮ የታደሙትን (በትንቢት አስቀድመው የሚያውቁትን) እነሆ ድግስን አዘጋጅቻለሁ (ወንጌል ተሠርጋለች) ኮርማዎቼ የሰቡት ከብቶቼ ታርደዋል፤ ሁሉም ተዘጋጅቶአል፤ (ምግበ ሥጋ፤ ምግበ ነፍስ፤ ሕይወተ ሥጋ፣ ሕይወተ ነፍስ ተሰጥቷል። መሲሑ ይሰቀላል፣ ይሞታል፣ በሥጋውም መቆረስ በደሙ መፍሰስ ሕይወት ታገኛላችሁ) ወደ ሠርጉ ኑ በሉአቸው ብሎ ላከ። አሁንም ወደየግል ሥራቸው (በሥጋ ፈቃዳቸው በመመራት) በመሄድ ካለመምጣታቸውም በተጨማሪ የተላኩትን አሽከሮች ይዘው አንገላቷቸው ገደሏቸም (ማቴ ፳፩፥፴፭-፴፰ ካለው ጋር ያነጻጽሩ)። ንጉሡም ተቆጣና ወታደሮቹን በመላክ የእንቢተኞችን ከተማ አቃጠለ (ወርቅ ያሸናፊው ምሳሌ ስለሆነ ነው እንጂ ድግስ ካልበላችሁ ብሎ ሰፈር የሚያቃጥል ኖሮ አይደለም። መሲሕን ያልተቀበሉት ሕዝበ አይሁድ የደረሰባቸውን መከራ አስቀድሞ መግለጹ ነበር) ወደ ሠርጉም ማንኛውም ሰው በመንገድ ወድቆ ከሚለምን ፅኑስ በዙፋን እስካለ ንጉሥ የተገኘው ሁሉ መጥቶ እንዲጋበዝ ያገኛችሁትን አምጡ ብሎ አሽከሮቹን አዘዘ። ለታደሙት ባይሳካላቸው መንገደኞች መጥተው የሠርጉን ቤት ሞሉት (እስራኤል ብታምጽ ይሁዳም ብትወናበድ፣ ካህናተ ኦሪት ቢክዱ፣ ፈሪሳውያን በወኃቸው ቢታሰሩ፣ ወንጌል ተማሪ አላጣችም። የንጉሡ ሠርግ ተደግሶ አይቀርም፤ ወንጌል እውን ሆና ትሰበካለች) ቤቱም በመጡት ሰዎች ሞላ። ንጉሡም ወደ ሠርጉ ቤት የመጡትን ሰዎች ለማየት በገባ ጊዜ የሠርጉ ቤት ሞልቶ ነበር (በሉቃስ ወንጌል «ወአዲቦ መካን» ገና ቦታ አለ የሚል አለ፤ መንግሥተ እግዚአብሔር ለሁሉም እንደምትበቃ ያሳያል) ወደ ሠርጉ ቤት ከገቡት መካከል የሠርግ ልብስ ባለመልበስ የተገኘው አንዱ ሰው ከሠርጉ እንዲወጣ ተደረገ ይላል።

ከመምህር ልዑለ ቃል አካሉ ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ፩ኛ መጽሐፍ የተወሰደ

EthiOrthodox e-mail Outreach EthiOrthodox@AOL.COM

ዛሬ የተነበበው ወንጌል በአጭሩ ከላይ የተጠቀሰውን ይመስላል።

መልእክት ለውድ አንባቢ፤ ሠርጉን ያዘጋጀው ንጉሥ እግዚአብሔር ነው። ሠርጉ ደግሞ ሙሽራይቱ ቤተ ክርስቲያን ሙሽራው ክርስቶስ አንድ የሚሆኑባት ወንጌል ናት።

ወደ ሠርጉ የታደሙት፤
፩ኛ) ትንቢት የተነገረላቸው ሱባኤ የተቆጠረላቸው፣ ተስፋ ያላቸው፣ የአብርሃም ዘሮች ሲሆኑ፤
፪ኛ) በአብርሃም ዘር ይባረካሉ የተባሉት የአሕዛብ ዘሮች ናቸው። የታደሙትን እንዲጠሩ የተላኩት የሚመጣውን ክርስቶስን እንዲቀበሉት የሰበኩ ነቢያት፣ የመጣውን ክርስቶስን እንዲያምኑ ያስተማሩ ሐዋርያት ናቸው።
፫ኛ) የተላኩት ደግሞ ተላውያነ ነቢያት ደቂቀ ነቢያት ተላውያነ ሐዋርያት፣ አርድእት እና መምህራን ናቸው። ድግሱ ደግሞ በኦሪት በወንጌል የተደረገው ተአምራት ነው።

እምቢተኞቹም፤
፩ኛ) በወጋቸው በሥርዓታቸው እያመካኙ ከመሲሑ የተለዩ ሕዝበ እስራኤል እንዲሁም በፍቅረ ጣዖት ተይዘው በሐጸ ዝሙት ተነድፈው ከፍቅረ እግዚአብሔር ወጥተው የዕለት ተለት ኑሮን ከክርስቶስ ጋር የሚያወዳድሩ ወይም የሚያስበልጡ፣ የሚያስቀድሙ አሕዛብ ሰብአ ዓለም ናቸው። እነዚህ ሰዎች በተለያየ ምክንያት ከእግዚአብሔር ማዕድ ራቁ፤ በፍቅረ ጣዖት ኃጢአት ወደቁ።

፪ኛ) በየመንገዱ እየተጠሩ መጥተው ወደ ሠርጉ ቤት የገቡት «እሬስዮ ሕዝብየ ለዘኢኮነ ሕዝብየ ወእሬስያ ፍቅርትየ ለእንተ ኢኮነት ፍቅርትየ» ትርጉሙም «ሕዝቤ ያልሆነውን ሕዝቤ አደርገዋለሁ፤ ፍቅረኛዬ ያልነበረችውን ወዳጄ አደርጋታለሁ» ተብሎ በሆሴእ የተነገረለት በአብርሃም ዘር እንደሚባረክ «ወበዘርእከ ይትባረኩ ኵሎሙ አሕዛብ ምድር» ትርጉሙም «በዘርህ የምድር አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ» የተባለለት የዓለም ሕዝብ ነው። የተገኘውም በጫካ በመንገድ፣ ጣዖት ሲያመልክ፣ በደል ሲፈጽም፣ ሞት ጸንቶበት፣ ፈተና በዝቶበት፣ ኩነኔ አይሎበት ነው። የወንጌል መልእክተኞችን ድምጽ ሰምቶ የሠርጉን ቤት ሞላው። ወደ ሠርጉ ቤት ያልመጡት አገልጋዮቹን ያልተቀበሉት፣ ሕዝብ፣ ከተማና መንደር በንጉሡ ትእዛዝ ተቃጠሉ፤ ነቢያትን በገደሉ ላይ የፋርስ፣ የባቢሎን ነገሥታት፤ ሐዋርያትን በገደሉ ላይ ሰብአ አርድእትን በገደሉ ላይ፣ የሮምን ነገሥታት አስነስቶ አገራቸውን በእሳት አቃጠለ። ሰዎቹንም አስማረከ። የንጉሥ ግብዣ የልጁ ሠርግ ድግስ፣ ወንጌል ግን ተማሪ አላጣችም። አሮጌ የለበሱት ተባረሩ፣ የሠርጉ ቤት መንግሥተ ሰማያት ጌጦችዋ ምእመናን ናቸው። በነሱ ሞላች፣ ንጉሡም ደስ አለው።

ዛሬም ወደዚህ ሠርግ ቤት ሁላችን ተጠርተናል። ጥሪውን እናክብርና እንሂድ። ሕይወታችን ለሞት አካላችን ለመቅሰፍት እንዳይሰጥ ዛሬም የንጉሡ ሠርግ ተደላድሏል። ሙሽራው መቼም መች ሙሽራ ነው፤ ሁላችን ወደ ወንጌል ተጠርተናል። ማንም በሚስቱ አመካኝቶ ከወንጌል የሚርቅ፤ በባልዋ አመካኝታ ከመሲሑ የምትርቅ፤ በሐብት፣ በንብረት፣ በልጅ፣ በቤት፣ በሥራ፣ በትዳር፣ በኑሮ አመካኝቶ የመሲሑን ልዑካን ቃል ጥሎ ከመሲሑ ሠርግ የሚቀር ቢኖር እጣ ፈንታው ሞት ነው። በዘመናችን የሰው ልጅ እግዚአብሔርን የሚያመልክ በጣም ሲሞላለት ወይም በጣም ሲጎድልበት ነው። ራሱን የሚያስማራበት ካገኘ ግን ከፈጣሪው ይርቃል፤ ወደ ንጉሡ የተጠሩት ሁሉም ናቸው። ከአይሁድ ወገን፣ ከካህናቱ፣ ሌዋውያኑ፣ ጸሕፍቱ፣ ፈሪሳውያኑ፣ ትልቅ ትንሹ፣ ወንዱ ሴቱ ነው።

ከአሕዛብ ወገንም የጣዖቱ ካህን፣ ሴቱ፣ ወንዱ፣ ትልቁ፣ ትንሹ፣ ሁሉም ነው። ዛሬም እኔን አይመለከተኝም የሚል አገልጋይ ቄስ፣ ሕዝብ፣ መምህር፣ ደቀ መዝሙር የለም። ሁሉም ተጠርቷል።

ቤቱ፣ ሕይወቱ፣ ሀገሩ፣ ንብረቱ በእግዚአብሔር መአት እንዳይጠፋ ንሰሐ መግባት አስፈላጊ ነው። በነቢያት ላይ፣ በሐዋርያት ላይ ስድብ ያበዙ ድንጋይ የወረወሩ ዛሬም ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ አምልተው አስፍተው በሚሰብኩ የቤተ ክርስቲያን መምህራን ላይ ድንጋይ ከመወርወር፣ ስም ከማጥፋት ዝም አላሉም። የአባቶቻቸው ልጆች ናቸውና እግዚአብሔር በቁጣው አይቀስፋቸው፤ ምሕረቱን ያብዛላቸው፤ ታመዋልና ይማራቸው።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ... አሜን።